# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 332 መስከረም 10 2007


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የህወሓት ስርዓት በሁለገብ ትግል ለመስወገድ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በመሆኑም የህዝብ ወገኖች በሙሉ ትኩረታችንን ወያኔ ላይ ብቻ እናድርግ። የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ እምቢ በማለት ስርዓቱን ከጫንቃችን አውርደን ለመጣል በሚደረገው ትግል ላይ እንድንረባረብ ግንቦት 7 ጥሪውን ያቀርባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በህወሓት አገዛዝ በኦጋዴን ሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የጅምላ ግድያ በጽኑ እናወግዛለን!!

የግንቦት 7 መግለጫ መስከረም 7 ቀን 2007 ዓ.ም.

የአገራችን የኢትዮጵያን በትረ ሥልጣን በጠመንጃ ኃይል የተቆጣጠረው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሥልጣን እድሜውን ለማራዘም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየወሰደ ያለውን እሥራትና ግድያ አጠናክሮ መቀጠሉን የሚያጋልጡ ማስረጃዎች በየጊዜው ከራሱ ከአገዛዙ እየሾለኩ በመውጣት ላይ ናቸው።

መስከረም 5 ቀን 2007 ዓም በኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥን በምስል ተደግፎ የቀረበው በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ ከነዚህ ማስረጃዎች አንዱ ነው ።

የወያኔን አገዛዝ ይቃወማሉ የተባሉና በኦጋዴን ክልል ከሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች ጋር ንኪኪ አላቸው የተባሉ እነዚያ የጅምላ ጭፍጨፋ ሰለባ የሆኑ ምስኪን ዜጎች አስከሬን መሬት ለመሬት እየተጎተተ አንድ ቦታ እንዲከማች ሲደረግ፤ አስከሬኑን ለመሰብሰብ ከታዘዙት የአካባቢው ነዋሪዎች አንዱ የገዛ ወንድሙ አስከሬን ከሚጎተተው መሃል እንደነበረ መስማት ህሊናን የሚሰቀጥጥና የወያኔ የጭካኔ እርምጃ አቻ የሌለው ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመላክት ነው።

በደርግ ዘመን ቤተሰብ የተገደለበትን ሰው አስከሬን ለማግኘት የጥይት ዋጋ ለመክፈል ይገደድ ነበር በማለት ሥርዓቱን በነጋ በጠባ የሚወነጅል አገዛዝ ከሚወነጅላቸው ሥርዓት በባሰ በኦጋዴን የገደለውን ንጹህ ዜጋ አስከሬን የገዛ ወንድሙ መሬት ለመሬት እንዲጎትተው አድርጓል። በዚህም ህወሓት በሰብዓዊነት ላይ ከቀደምቶቹ ሁሉ የከፋ የሚሰቀጥጥ ወንጀል ፈጽሟል። ቀደም ሲል በበደኖ፤ በአርሲ፤ በአርባ ጉጉ፤ በሃዋሳ፤ በጋምቤላ እና ድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባና ሌሎች የአገሪቱ ከተሞች ነዋሪዎች ላይ በወያኔ ልዩ ትዕዛዝ ተመሳሳይ የጅምላ ጭፍጨፋዎች ተካሂደዋል። ይህ ሁሉ ወንጀል እየተፈጸመብን አስከዛሬ ወያኔን በጫንቃችን ተሸክመን ለመኖር የተገደድነው እነዚሁ ጥቂት ዘረኞች ሕዝባችንን በዘር፤ በቋንቋና በሃይማኖት በመከፋፈላቸው አንዱ የኅብረተሰብ ክፍል ሲጠቃ ሌላው በዝምታ የሚመለከትበት ሁኔታ በመፈጠሩ ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በኦጋዴን ሕዝብ ላይ የፈጸመውን ይህንን አረመኔያዊ እርምጃ አጥብቆ ያወግዛል። ጊዜው ሲደርስ የዚህ ወንጀል ፈፃሚዎች ለፍርድ መቅረብ አለባቸው ብሎ ያምናል። ስለሆነም ወያኔ ሕዝባችንን አቅም ለማሳጣት ላለፉት 23 አመታት በኅብረተሰባችን መካከል የገነባውን የጥርጣሬና የጥላቻ ግንብ በመናድ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በኦጋዴንና በሌሎች የአገራችን ክፍሎች ወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰቆቃና እልቂት ለማስቆም እንዲችሉ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

ኦጋዴን ውስጥ ለፈሰሰው የንጽሃን ደምና በሰብዓዊነት ላይ እየተፈጸመ ላለው ወንጀል ተጠያቂው ሥልጣንን በኃይል የሙጥኝ በማለት በአገርና በሕዝብ ሃብት ዘረፋ ላይ የተሰማራው ጥቂት የህወሃት አመራር መሆኑ አያጠያይቅም። ይህንን ወንጀለኛ ቡድን ለፍርድ ለማቅረብ ንቅናቄዓችን ግንቦት 7 የሚያደርገውን ሁለገብ ትግል ለፍትህ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የቆመ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲቀላቀል በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ቀርቦለታል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አለም አቀፉ የግንቦት 7 "ላንች ነው ኢትዮጵያ" ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ

በሰሜን አሜሪካ፤ ካናዳ፤ አውስትራልያ፤ አውሮጳ እንዲሁም አፍሪካ የተለያዩ ግዛቶችንና ከተሞችን በማዳረስ የተዘጋጀው "ላንች ነው ኢትዮጵያ!" የግንቦት 7 አለማቀፍ አመታዊ ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ ባሳለፍነው እሁድ ሴፕቴንበር 14 ቀን በቤልጂም ብራስልስ በተካሄደው ደማቅ የመዝጊያ ስነ ስርአት ተጠናቀቀ። የመጨረሻዎቹ ዝግጅቶች ባሳለፍነው ቅዳሜ ሴፕቴንበር 13 በኔዘርላንድ አምስተርዳም፤ በስዊዘርላንድ በርን እንዲሁም በሴፕቴንበር 14 በቤልጂሟ ብራስልስ ከተማ እጅግ በደመቀ ሁኔታ መካሄዳቸውን ከስፍራው የተላከልን መረጃ ያመለክታል። በዝግጅቶቹ ላይ በክብር እንግድነት በመገኘት ከኢትዮጵያውያን ጋር ምክክር ያደረጉት የግንቦት 7 አመራሮች በአምስተርዳምና ብራስልስ አቶ አበበ ቦጋለ ሲሆኑ በበርን አቶ ብዙነህ ፅጌ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የግንቦት 7 "ላንች ነው ኢትዮጵያ" አለማቀፍ ዝግጅት እጅግ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ከንቅናቄው የተላካለን መረጃ ያመለክታል። በየ ዝግጅቶቹ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የግንቦት 7 አመራሮች የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔቶች በተመለከተ፤ የጉጅሌው ወያኔን ማስወገድ በሚቻልባቸው የትግል ስልቶች እንዲሁም በአሁኑ ሰአት በፋሽስቶች እጅ ወድቆ ስቃይ እየተፈጸመበት የሚገኘውን የትግል ጓዳችንን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በተመለከተ እጅግ ስኬታማ ሊባል የሚችል ውይይት ማድረጋቸውን ንቅናቄው ገልጿል። ከየመን ሰንአ አየር ማረፍያ በህገወጥ መንገድ ታፍነው ለጉጅሌዎቹ ተላልፈው የተሰጡት የንቅናቄያችን ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስራዎች በቪዲዮና በምስል ተዘጋጅተው በየዝግጅቶቹ ላይ ለዕይታ የቀረቡ ሲሆን የነፃነት አርበኛው ስራዎች ኢትዮጵያውያኑ ላይ ቁጭትን በመፍጠር ለመጭው ትግል በቁርጠኝነት ታጥቀው እንዲነሱ ያደረጉዋቸው ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## በጋምቤላ ዉስጥ የተቀሰቀሰው ግጭት ተባብሷል፤ አካባቢው ከፍተኛ ውጥረት ላይ ነዉ

በጋምቤላ ክልል በጎደሬ ወረዳ መጢ ከተማና አከባቢው ከ 24 አመታት በላይ የኖሩ የአማራና የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን አከባቢያችን ለቅቃችሁ ውጡ በሚል ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ግጭት ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ በአካባቢው ውጥረት መንገሱን ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱ የፋሽስቱ ወያኔ ከፋፍለህ ግዛ ውጤት መሆኑን የሚናገሩት ታዛቢዎች ሁሉም በአካባቢው የሚኖሩ የተለያዩ ብሄረሰቦች በሰላምና በፍቅር ተቻችለው ለዘመናት ይኖሩ እንደነበር ተገልጿል። አሁን ላይ በተቀሰቀሰው ደም አፋሳሽ ግጭት ከ10 በላይ ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ገዳዩቹ በአከባቢው ከጉጅሌው ወያኔ ሹማምንቶች ጋር በንግድና እርሻ ስራ ላይ በሽርካነት የሚሰሩ ገለሰቦች እንዲሁም የታጠቁ የአገዛዙ ቅጥረኛ ፖሊሶችና የአካባቢው ሚሊሻዎች እንደሆኑ ምንጮቻችን አመልክተዋል። ግጭቱ ሆን ተብሎ በፋሽስቱ ወያኔ የተቀሰቀሰ ሴራ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው ለዘመናት ይኖሩ የነበሩት እኒሁ ብሄረሰቦች ግጭቱ ለመሸሽ ወደ አጎራባች ከተሞች ሸሽት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱ አሁንም ድረስ እንደቀጠለና በአካባቢው ውጥረት መንገሱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተለይ በሽሽት ላይ ያሉት ወገኖች የድረሱልን ጥሪ ማሰማታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ ዜና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ለአንድ ሳምንት ያህል ሊሰጥ የታሰበው እና የተጀመረው የፋሽስቱ ወያኔ የልማታዊ ዲሞክራሲ ስልጠና ገን ከጅምሩ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደገጠመው የውስጥ ምንጮቻችን የላኩልን መረጃ ያመለክታል። ስልጠናው ከመጀመሩ መምህራኑ አገዛዙ ያለብንን ችግር እንዲሁም በአገሪቱ ላይ የጋረጠውን የመበታተን አደጋ እንዲሁም ሁለንተናዊ ችግር መፍታት ካልቻለ የስራ ማቆም አድማ እናደርጋለን ሲሉ መዛታቸው ታውቋል። ይህ የግዳጅ ስልጠና በተለያዩ ቦታዎች መሰጠት መጀመሩን ያደረሱን የውስጥ ምንጮቻችን የውይይቱ የመግቢያ ሰነድ ተረስቶ በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ እና በመምህራን ሕይወት ዙሪያ በተነሳ የውይይት አለመግባባት ሲናጥ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ስልጠናውን እንዲመሩ ሃላፊነት የተሰጣቸው የፋሽስቱ ቅጥረኞች ገና ከጅማሬው ከመምህራኑ የሚሰነዘርባቸውን ጥያቄ እንዲሁም ተቃውሞ ማስተናገድ ባለመቻላቸው መምህራኑ ላይ ማስፈራሪያና ዛቻ እንዳደረሱባቸው ታውቋል።

## የወያኔውን የከፋፍለህ ግዛ ስርዓት ለመጣል በአንድነት እንነሳ!!!

ዛሬም እንደ ትናንቱ ምንም የማያውቁ ህጻናት ዋይታ!!! የሴቶችና አረጋዊያን ሌላ ዙር መፈናቀል! ሌላ ዙር የጅምላ ስደት መራር መርዶ ከወደ ጋምቤላ

የግጭቱ ስረ መሰረት እንዲህ ነው። የህወሓት አገዛዝየአካባቢውን ማኅበረሰብ በማፈናቀልና ለም መሬታቸውን ቀምቶ በኢንቨስትመንት ስም ባብዛኛው ካንድ አካባቢ ለመጡ የወያኔ አባላት ቀደም ሲል ለሰሩት ወንጀል ማካካሻ እንዲሆን ታስቦ ካቅማቸው በላይ ቸራቸው። እነሱም ያለምንም ይሉኝታና ያካባቢውን ማኅበረስብ ያኗኗር ሁኔታ በጭራሽ ከግምት ሳያስገቡ ጌታዋን እንደተማመነች በግ ያካባቢው ማኅበረሰብ ለዘመናት ሲወርድና ሲዋረድ ጠብቆ ያቆየውን ጥብቅ ደን እየመነጠሩ የጣውላና የከሰል ንግድ ላይ ተሰማሩ።

የአካባቢው ማኅበረሰብ ግን የበይ ተመልካች ሆነ፣ ቅሬታውን ለባለስልጣናት አቤት ቢልም ሰሚ አላገኘም። ጭራሽ ይባስ ብለው በቀየው የተገኘውን ሴት ወንድ ሳይመርጡ በፌደራል ፖሊስ በመቀጥቀጥ ብዙዎችን ለሞት ሲዳርጓቸው ሌሎችን ደግሞ ቁስለኛ አድርገዋል። ከሞትና ከመቁለት የተረፉትም ተፈናቅለው ዱር ገደሉን ቤታቸው አድርገዋል። በሌላም በኩል የግጭቱ ሰለባ የሆኑት ከሌላ ክልል መጥተው ለረዠም ጊዜ ባካባቢው ኑዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊን ዜጎችም የግጭቱ ሰለባ ከመሆን አልተረፉም፣ እነሱም ሞትና ቁስለኛ ሆነዋል። ከሞትና ከመቁሰልም የተረፉት በቴፒ ከተማ አውላላ ሜዳ ላይ ተበትነው ምንም የማያውቁ ሴቶችና ህጻናት ቀን በጸሀይ ሌሊት በቁር እየተጠበሱ ይገኛሉ። እጅግ የሚያሳዝነው ግጭቱን የሚባብሱትና በዋና ተዋናይነት የሚተውኑት የወያኔው ቅጥረኞች የሆኑ የአካባቢ ካድሬዎችና መሬቱን ያላግባብ የቀሙ ያንድ አካባቢ ተወላጆችና ያንድ አካባቢ የፌደራል ፖሊስና የመከላከያ የበላይ ሹማምንት መሆናቸው ነው።

እንዲህ ዓይነቱ የወያኔ ሴራ ዛሬ የተጀመረ አዲስ ክስተት አይደለም። ህወሓት ገና ከመጀመሪያው ሲፈጠር አብሮት የነበረና ላለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት የቀጠለ እዳ ነው። ይህ ህወሓት ኢትዮጵያዊያንን እርስ በራስ በማጋጨት ለዘመናት ለመግዛት አስቦና አልሞ የተነሳበትና ከኢጣሊያን ቅኝ ገዝ የተማረው ስልት ነው፤ ይህ የህወሓት ባንዳነት ውጤት ነው።

ባለፉት አመታት በጉራ ፈርዳና በቤንሻንጉል ክልል የተፈናቀሉትን ኢትዮጵያዊን ለዘመናት ከኖሩበት ስፍራ ሲፈናቀሉ ያየነውም ይህንኑ የፋሽስታዊ ስርዓታቸው መገለጫው የሆነውን ዘር ለይቶ ማፈናቀልና ማሳደድን ነው።

በጋምቤላ ክልል በሜጢ ከተማና አካባቢው የንጹሀን ዋይታና ሰሚ ያጣ ጩኸት ሁላችንንም፤ ማለትም ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ በእጅጉ ሊያሳስበንና ይገባል። በቶሎ ባንድነት ተረባርበን ካላስቆምነው መዘዙ የምንወዳት ሀገራችንን እንዳልነበረች ሊያደርግ የሚችል አደገኛ ሁኔታ ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን ተገነዝቦ ስርዓቱን በሁለገብ ትግል ለመስወገድ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በመሆኑም የህዝብ ወገኖች በሙሉ ትኩረታችንን ወያኔ ላይ ብቻ እናድርግ። የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ እምቢ በማለት ስርዓቱን ከጫንቃችን አውርደን ለመጣል በሚደረገው ትግል ላይ እንድንረባረብ ግንቦት 7 ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !**

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ መምህራንን አስገድዶ ማሰልጠኑን ተያይዞታል

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ካለፈው ሰኞ ጀምሮ ለመምህራን መስጠት የጀመረው አስገዳጅ ስልጠና በከፍተኛ ተቃውሞ እየተናጠ መቀጠሉን የውስጥ ምንጮቻችን የላኩልን መረጃ ያመለክታል። በልማታዊ ዲሞክራሲ፤ በፖሊሲና እቅድ አተገባበር ዙሪያ ለአንድ ሳምንት ያህል አገዛዙ ሊሰጥ በጀመረው ስልጠና ላይ ተቃውሞ መበርታቱን ተከትሎ በአሰልጣኝነት የተመደቡ የወያኔ ቅጥረኞች ጭምር ግራ መጋባታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በተለይ ከወደ አማራ ክልል የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራኑ የጉጅሌው ወያኔ ያለብንን ችግር እንዲሁም በአገሪቱ ላይ የጋረጠውን የመበታተን አደጋ እና ሁለንተናዊ ችግር በአስቸኳይ እልባት መስጠት ካልቻለ በዚህ በያዝነው የ 2007 የስራ አመት የስራ ማቆም አድማ እናደርጋለን ሲሉ መዛታቸው ታውቋል። በአብዛኛው የስልጠና ቦታዎች ገና ከጅማሬው የስልጠናው የመግቢያ ሰነድ ተረስቶ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ እና በመምህራን ሕይወት ዙሪያ በተነሳ የውይይት አለመግባባት ሲናጡ እንደነበር ምንጮቻችን አመልክተዋል።

በስልጠናው ላይ የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጥያቄ ጋር በተያያዘ በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል በተደረገው ተቃውሞ ላይ የወያኔው አጋዚ ጦር በንፁሃን ዜጎች ላይ የወሰደውን አሰቃቂ የግድያ እርምጃ አስመልክቶ የሰጡት በቅጥፈት የታጨቀ አስተያየት በመምህራኑ ዘንድ ከባድ ተቃውሞ ማስነሳቱንም ለማወቅ ችለናል። ስልጠናውን በመስጠት ላይ የሚገኙት የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንት በኦሮሚያ ክልል የተካሄደውን የተቃውሞ ድምጽ ያሰሙ ሰዎች በጠባብነት የሚታወቁ አካላት ናቸው በማለት፤ የተወሰደውን የግድያ እምጃም ተገቢ ነው ሲሉ አስተያየት መስጠታቸው ታውቋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ት/ቤቶች በመሰጠት ላይ ያለው ስልጠናም ገና ከጅማሬው አለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት እየተስተጓጎለ እንደሚገኝ ታውቋል። በመምህራኑ መቅረብ የጀመረው ቅሬታና ተቃውሞ በአገዛዙ ቅጥረኛ አሰልጣኞች ዘንድ ጭምር እርስ በርስ አለመግባባት መፍጠሩንም ምንጮቻችን ገልጸዋል።

## በሶማሊ ክልል የተፈጸመው የጅምላ ግድያ ” ፋሽስቱ ወያኔ ለህዝብ ያለውን ንቀት ያሳያል” ተባለ

የቀድሞው የሶማሊ ክልል ፕሬዚዳንት የህዝብ ግንኙነት ስራ አማካሪ እና የክልሉ የወጣቶች ሊቀመንበር በመሆን ካገለገለ በሁዋላ የተለያዩ የቪዲዮ ማስረጃዎችን በመያዝ ከአገር የወጣው ወጣት አብዱላሂ ሁሴን ፣ “አ አጋዴን” በሚል ኢሳት ያስተላለፈው አጭር የዶክመንታሪ ፊልም፣ በስልጣን ላይ ያሉት ገዢዎች ለሶማሌ፣ ለኢትዮጵያና በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ያላቸውን ከፍተኛ ንቀት ያሳያል ሲል ለኢሳት ገልጿል።

ዘገባውን ከተመለከተ በሁዋላ ህመም እንደተሰማው የገለጸው አብዱላሂ፣ አስከሬን እንዲለቅሙ ሲገደዱ የነበሩት ሲቪሎች ሁኔታ በእጅጉ እንደረበሸው ገልጿል። አያይዞም ወጣት አብደዱላሂ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን አስወግደው በአንድነት በመነሳት በስልጣን ላይ ያለውን ሃይል ማስወገድ እንደሚገባቸውም መልእክት አስተላልፏል።

የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻ አውጭ ግንባር /ኦብነግ የአማርኛ ክፍል ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ ሃሰን አብዱላሂ በበኩላቸው፣ በክልሉ የሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት የቆየ መሆኑን ገልጸው፣ ድርጅታቸው በደቡብ አፍሪካ፣ በሄግ፣ በስዊድንና በጄኔቫ ጉዳዩ ተጣርቶ ተጠያቂ የሚሆኑት የወያኔ ሹማምንትን በህግ እንዲጠየቁ አቤቱታ ማቅረባቸውን ለኢሳት ገልጸዋል።

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የተገደሉት የኦብነግ አባላት እንጅ ሲቪሎች አይደሉም በሚል ለማስተባበል ቢሞክር የእናንተ ምላሽ ምን ይሆናል ተብለው የተጠየቁት አቶ ሃሰን፣ አገዛዙ በራሱ የሚተማመን ከሆነ አካባቢውን የጦር ቀጠና ማድረጉን ትቶ ለውጭ ጋዜጠኞችና የሰአብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ክፍት ማድረግ አለበት በማለት፣ በክልሉ የሚፈጸመው ጥቃት በንጹሃኑ ህዝቡ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ዶክመንታሪ ፊልሙ ለእይታ ከበቃ በኋላ ኢትዮጵያውያን በማህበራዊ ድህረ ገፆች ፋሽስቱ ወያኔ የፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ እያወገዙ ሲሆን ለተገደሉ ንፁሃን ዜጎችና ለተጎጂ ቤተሰቦች ሃዘናቸውን በመግለጽ ላይ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።

## የኦጋዴን ኡኡታ

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በወጣትነታችን ብረት አንስተን ጫካ እንድንገባ አደረገን ብለዉ የሚናገሩት በወቅቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተንሰራፍቶ ይታይ የነበረዉ በብሄር ብሄረሰቦች ጭቆና ነበር። ወያኔዎች በለስ ቀንቷቸዉ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላም ቢሆን ለእነሱ ለራሳቸዉ የሚመች ህገ መንግስት ጽፈዉ ትልቁን የኢትዮጵያ ችግር ፈታን ብለዉ የሚናገሩት ይህንኑ ዛሬም ድረስ እናት አገራችንን ኢትዮጵያን እንደ ነቀርሳ በሽታ ቀስፎ ይዞ የሚቆጠቁጣትን የብሄር ብሄረሰቦች ችግር ነዉ። ወያኔ በ1994 ዓም ህገመንግስቱን አጽድቆ የፌዴራል ስርዐት ከመሰረተ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጎ የጮኸዉ ማንም መፍታት ቀርቶ ሞክሮት እንኳን የማያዉቀዉን የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ችግር እኔ ፈታሁት የሚል ለሱና ለደጋፊዎቹ ብቻ የሚሰማ ጬኸት ነበር። ወያኔ የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ከታሰሩበት ሰንሰለት ፈትቼ "ነፃ" አወጥቼ እራሳቸዉን በራሳቸዉ እንዲመሩ መንገድ ከፈትኩላቸዉ ብሎ ከተናገረ ከሃያ አመታት በኋላ ዛሬም ኢትዮጵያ ዉስጥ የትኛዉም ብሄረሰብ እራሱን በራሱ ማስተዳደር ቀርቶ የአገሪቱ ዜጎች ባሰኛቸዉ ቦታ መኖር እንኳን አይችሉም። የሚገርመዉ ነጻነትና እኩልነት የሠላም ጠላቶች የሆኑ ይመስል ዛሬ ወያኔ ነጻ ወጡ የሚላቸዉ ብሄረሰቦች በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ የሚታየዉ የአገራችንን አንድነት ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ብጥብጥ፤ ግጭትና ክልሌን ለቅቀህ ዉጣ የሚል ወያኔ ይዞብን የመጣዉ መፈክር ነዉ።

ወያኔ ጫካ ዉስጥ እያለ ደርግን በተደጋጋሚ በዘር ማጥፋት ወንጀል ይከሰስ እንደነበር ያኔ ወያኔ ምን ይዞልን ወይም ይዞብን ይመጣ ይሆን እያልን እንከታተለዉ ለነበርን ኢትዮጵያዊያን የቅርብ ግዜ ትዝታችን ነዉ። ከወያኔ ዉንጀላዎቹ አንዱና ዋነኛዉ ደግሞ ወያኔ እራሱ አቀነባብሮና አዘጋጅቶ ሐዉዜን ዉስጥ በቪድዮ እየተቀረጸ የተካሄደዉ ዉጊያ ነበር። በዚህ ዉጊያ ላይ ደርግ በአዉሮፕላንና በታንክ እየታገዘ መንደሮችን በመደምሰስ ብዙ ሰላማዊ ዜጎችን እንደጨረሰ ወያኔ ዛሬም ድረስ የሚነግረን ዉንጀላ ነዉ። የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያዉቀዉ የማይፈልጉትና እነሱም በፍጹም የማይነግሩን እዉነት ቢኖር ደርግን አሸንፈዉ አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ ከደርግ የወረሱት እነሱ እንደሚሉት ባዶ ካዝና ብቻ ሳይሆን የደርግን ክፋት፤ ጭካኔና ጭፍጨፋ ጭምር መሆኑን ነዉ።

ዘረኞቹአ የወያኔ መሪዎች ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸሙትን ወንጀል መዘርዘር እራሱን የቻለ ትልቅ ፕሮጀክት ነዉና ዛሬ ወደዚያ አንሄድም፤ ሆኖም ይህ ዘረኛ ቡድን ነኝ ብሎ የሚናገረዉን አለመሆኑን ለማሳየት ስንል ብቻ ሁለቱን ትላልቅ የወያኔ የሰዉ ዘር ማጥፋት ወንጀሎች መናገሩ ፍሃዊ ይመስለናል። የወያኔ ዘረኞች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ከፈጸሟቸዉ ወንጀሎች አንዱና ትልቁ በታህሳስ ወር 1996 ዓም በአኘዋክ ህዝብ ላይ የፈጸሙት የሰዉ ዘር ማጥፋት ወንጀል ሲሆን ሌላዉ ደግሞ አሁንም ድረስ እልባት ያላገኘዉና ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ በሶማሌ ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት አይን ያወጣ ጭፍጨፋ ነዉ። ፋሺስቱ ደርግ በአዉሮፕላንና በጦር ሂሊኮፕተሮች እየታገዘ ህፃን፤ አዋቂ፤ ሴትና ወንድ ሳይለይ ህዝብ ይጨፈጭፋል እያለ ሲከስ የነበረዉ ወያኔ ዛሬ እሱ እራሱ ከደርግ በከፋ ሁኔታ ኦጋዴን ዉስጥ እንዲህ ነዉ ተብሎ በቃላት ለመናገር የሚያዳግት ሰቆቃ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየፈጸመ ነዉ። ደርግን - ደርግ ለመሬቱ እንጂ መሬቱ ላይ ስለሚኖረዉ ህዝብ ደንታ የለዉም እያለ አምርሮ ይኮንን የነበረዉ ወያኔ የሱም ጉዳይ ኦጋዴን ዉስጥ አገኛለሁ ብሎ ከሚተማመነዉ የነዳጅ ኃብት ጋር እንጂ ከኦጋዴን ህዝብ ጋር እንዳልሆነ በተደጋጋሚ በዚህ ህዝብ ላይ በፈጸማቸዉና ዛሬም ድረስ በሚፈጽማቸዉ አረመኔያዊ የጭካኔ እርምጃዎች በተግባር አረጋግጧል። የሰላም፤ የፍህና የነጻነት ጠላት የሆነዉ ወያኔ ኦብነግን ከኦጋዴን ምድር አጠፋለሁ በሚል ሰበብ በክልሉ በየቀኑ በሚወስዳቸዉ ፀረ ህዝብ እርምጃዎች የብዙ ሠላማዊ ዜጎችን ደም እያፈሰሰ ነዉ።

በ1983 ዓም የሽግግሩ መንግስት ሲቋቋም የጀመረዉን የትጥቅ ትግል አቋርጦና የታጠቀዉን መሳሪያ አዉርዶ የሽግግሩን መንግስት ከተቀላቀሉት አማጽያን ዉስጥ አንዱ ኦብነግ በሚል ምህጻረ ቃል የሚታወቀዉ የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር ነበር። ይህ ግንባር በታህሳስ ወር 1984 ዓም ኦጋዴን ዉስጥ በተካሄደዉ የአካባቢ ምርጫ ከ80 በመቶ በላይ ድምጽ በማግኘት የክልሉን መንግስት መስርቶ የሽግግሩ መንግስት የስራ ዘመን እስካበቃበት ግዜ ድረስ ኦጋዴንን አስተዳድሯል፤ ሆኖም ክልሎች እራሳቸዉን ችለዉ በራሳቸዉ መርህና የፖለቲካ ፕሮግራም ሲመሩ ማየትና መስማት የማይወደዉ ወያኔ የኢትዮጵያ ሶማሌ ዲሞክራቲክ ሊግ የሚባል ተለጣፊ ድርጅት በመፍጠርና ይህ ተለጣፊ ድርጅት የ1987ቱን ምርጫ እንዲያሸንፍ በማድረግ ሰላም ፈልጎ የመጣዉን ኦብነግ ከጨዋታ ዉጭ በማድረግ ሌሎች አማራጮችን እንዲመለከት አስገድዶታል። በዚህ የወያኔ አሻጥርና የማግለል እርምጃ የተከፋዉና በሠላማዊ መንገድ ለኦጋዴን ችግሮች መፍትሄ ማግኘት ይቻላል በሚል እምነት ትጥቁን ፈትቶ የሽግግሩን መንግስት የተቀላቀለዉ ኦብነግ እንደገና ትጥቁን አንስቶ ጦርነት ዉስጥ ለመግባት ተገድዷል። የወያኔ መሪዎች ፍላጎትም ቢሆን በፌዴራሊዝም ስም በየክልሉ የራሳቸዉን አሻንጉሊቶች እያስቀመጡ በእጅ አዙር ክልሎችን በቁጥጥራቸዉ ዉስጥ ማድረግ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች እራሳቸዉን በራሳቸዉ እንዲያስተዳድሩ ማድረግ እንዳልሆነ በኦጋዴንና በሌሎችም ክልሎች የወሰዷቸዉ እርምጃዎች በግልጽ ያሳያሉ።

የደርግ ስርዐት በህዝባዊ አመጽ ተደምስሶ አዲስ አበባ ዉስጥ በ19983 ዓም የሽግግር መንግስት ሲቋቋም የኦብነግ መሪዎች ከመሳሪያ ትግል ይልቅ በሽግግር መንግስቱ ዉስጥ መሳተፍ ለመብቱና ለነጻነቱ እንታገላለን ለሚሉት የኦጋዴን ህዝብም ሆነ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይበጃል ብለዉ ጫካዉን ጥለዉ ከተማ መምጣታቸዉ የሚያሳየን አንድ ትልቅ ሀቅ ቢኖር ለትግል ያነሳሳቸዉ የፍትህ፤ የነጻነትና የእኩልነት ጥማት መሆኑን ነዉ። ኦብነግ ገዢዎችም ሿሚዎችም እኛ ብቻ ነን በሚሉ ስግብግብ የወያኔ መሪዎች ተገፍቶ የሚያስተዳድረዉን ህዝብ ጥሎ ጫካ ባይገባ ኖሮ ዛሬ ኦጋዴን የሰላም ቀጠና ሆና ኦጋዴንን ለማዉደም የሚወጣዉ ከፍተኛ ወታደራዊ ወጪ ለዕድገትና ለልማት ስራዎች ይዉል ነበር።

የወያኔን መሪዎች ተንኮል፤ አሻጥርና ራስ ወዳድነት ከኦብነግ መሪዎች በላይ የሚያዉቅ ማንም የለም። ሆኖም የኦብነግ መሪዎች መሠረታዊ ፍላጎት የኦጋዴን ህዝብ መብቱና ነጻነቱ ተጠብቆ ፍትህ በሰፈነባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በእኩልነት እንዲኖር ማየት ስለሆነ በወያኔ ዘረኞች ዕብሪትና ተንኮል ተስፋ ሳይቆርጡ ይህ ፍላጎታቸዉ ሊሳካ የሚችልበትን መንገድ በሰላማዊ መንገድ ለማሳካት አሁንም እንደጣሩ ነዉ። ወያኔ ግን ይህንን የኦብነግ መሪዎች የሰላም ፍላጎት እንደ ፍርሃትና ሞኝነት በመቁጠር በጎረቤት አገር መሪዎች አማላጅነት ለድርድር የመጡ የኦብነግ መሪዎችን ለድርድር ከሄዱበት ከናይሮቢ ከተማ አፍኖ ወደ አዲስ አበባ ወስዷል። የወያኔ መሪዎች እንደነዚህ አይነቶቹን ጭፍንና ፀረ ሠላም የሆኑ እርምጃዎችን በኦብነግና በሌሎችም ብረት ባነሱ ኃይሎች ላይ በመዉሰድ በአንድ በኩል በሠላማዊ መንገድ በዉይይትና ድርድር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን አላስፈላጊ ወደ ሆኑ አዉዳሚ ጦርነቶች እንዲያመሩ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የህዝብን ልብ በማስሸፈት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ሃምሳ ኪሎሜትር በማይሞላ ርቀት እራሳቸዉን "ነፃ አዉጭ" ግንባር ብለዉ የሰየሙ አያሌ ድርጅቶች ይገኛሉ። እነዚህ የዚህ ወይም የዚያ ብሄረሰብ ነፃ አዉጭ ግንባር ነን ባዮች የተፈጠሩት የወያኔ ዘረኝነት፤ ዕብሪትና ንቀት ትዕግስታቸዉን ባስጨረሰ ሰዎች ነዉ እንጂ የነዚህ ድርጅቶች መሪዎች እንመራዋለን የሚሉት ህዝብ ችግር ከተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ጋር አብሮ እንደሚፈታ ረስተዉት አይደለም።

የሰብዓዊ መብቶች ተንከባካቢ ወይም በፈረንጆቹ ቋንቋ ሂዩማን ራይትስ ዋች የተባለዉ አለም አቀፍ ተቋም እንደ ፈረንጆቹ አመን አቆጣጠር በሁለት ሺ ስምንት በመረጃ አስደግፎ ባወጣዉ ዘግናኝ ሪፖርት ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን ህዝብ ላይ የሚፈጽመዉን የጅምላ ቅጣት በግልጽ አሳይቶን ነበር። ሪፖርቱ ኦጋዴን ዉስጥ የመከላከያ ሠራዊት፤ ልዩ ፖሊስና የአካባቢዉ ሚሊሺያ ሠላማዊ ዜጎችን ከየመንደሩ እየጎተቱ የኦብነግ አባላት ናችሁ ብለዉ እንደሚረሽኑና ቤታቸዉን እንደሚያቃጥሉ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብና ለእኛ የጉዳዩ ባለቤት ለሆንነዉ ኢትአጵያዉያን አሳዉቋል። ይህ በቪድዮ ተደግፎ የቀረበዉ ሪፖርት እናት ልጇ ፊቴ ላይ ተረሸነ፤ አባት የልጆቼ እናት አይኔ እያየ ተደፈረች፤ ህጻናት ደግሞ አይናችን እያየ ወላጆቻችንን ተቀማን ብለዉ እያለቀሱ ሲናገሩ ያሳየን ሪፖርት ነበር። በወቅቱ ይህንን እጅግ በጣም ዘግናኝ የሆነ ቪዲዮ አይቶ ልቡ ያልተነካ ኢትዮጵያዊ አልነበረም።

ሂዩማን ራይትስ ዋች ይህንን ሪፖርት ይፋ ካደረገ ከስድስት አመታት በኋላ ዛሬም ወያኔ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽመዉን ለጆሮ የሚዘገንን ወንጀል ከመፈጸም ወደ ኋላ አላለም። እንዲያዉም ኦብነግን ከኦጋዴን ምድር ላይ ጠራርጌ አጠፋለሁ እያለ ግድያዉን፤ አፈናዉን ፤ ድብደባዉንና እስሩን በስፋት ቀጥሎበታል። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ዛሬም ኦጋዴን ዉስጥ ሠላማዊ ዜጎችን በዘፈቀደ ይገድላሉ፤ ወጣትና ህጻናት ሴቶችን ይደፍራሉ፤ መኖሪያ ቤቶችን ያቃጥላሉ። ባለፈዉ ማክሰኞ መስከረም አምስት ቀን የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን በቪድዮ አስደግፎ ባቀረበዉ ዘገባ የወያኔ መሪዎች ምን አይነት ጨካኞች፤ አረመኔዎችና ለሰዉ ልጆች ምንም አይነት ክብር የሌላቸዉ አዉሬዎች መሆናቸዉን በግልጽ አሳይተዉናል። የዛሬ ስድስት አመት ሂዩማን ራይትስ ዋች ባወጣዉ ሪፖርትና ከሰሞኑ ደግሞ ኢሳት ቴሌቪዥን ባቀረበዉ የግማሽ ሰዐት ሪፖርት ዉስጥ የኦጋዴን ዜጎቻችን አሁንም ለእርድ እንደሚጎተት እንስሳ ተጎትተዉ በጥይት እንደሚደበደቡ፤ የኦጋዴን ምድርም ካላይና ከታች በቦምብ እንደሚጋይ በአይናችን ተምልከተናል።በዚህ ሰዉ ሆኖ መፈጠርን በሚያስጠላ ቪዲዮ ዉስጥ የወያኔ አረመኔ መሪዎች ሠላማዊ ዜጎችን እንደ ቅጠል አርግፈዉ "ልቀመዉ" "አምጣና ደርድር" እያሉ የራሳቸዉን ዜጋ በጅምላ በገደሏቸዉ የራሳቸዉ ዜጎች አስከሬን ፊት ቆመዉ ደስታቸዉን ሲገልጹ ታይተዋል። ከዚህ በተጨማሪ አንደኛዉ ወያኔ የአስከሬኑን ጭንቅላት በቪድዮ ቅረጸዉ ሲል ሌላዉ ደግሞ ይሄኛዉ ጆሮዉ ተቆርጧል እያሉ በገደሏቸዉ ሰዎች ፊት ቆመዉ ሲሳለቁ ተሰምተዋል። በዚህም ወያኔዎች ከእነሱ ዉጭ የሆንዉን ኢትዮጵያዊያን በቁማችን ብቻ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ኦጋዴን ዉስጥ የተፈጸመው ግፍና በደል ገዢው ፓርቲ ለህዝብ ያለውን ንቀት ያሳያል" ተባለ

የቀድሞው የሶማሊ ክልል ፕሬዚዳንት የህዝብ ግንኙነት ስራ አማካሪ እና የክልሉ የወጣቶች ሊቀመንበር በመሆን ካገለገለ በሁዋላ የተለያዩ የቪዲዮ ማስረጃዎችን በመያዝ ከአገር የወጣው ወጣት አብዱላሂ ሁሴን ፤ "አ ኦጋዴን" በሚል ኢሳት ያስተላለፈው አጭር የዶክመንታሪ ፊልም፣ በስልጣን ላይ ያሉት ገዢዎች ለሶማሊ፣ ለኢትዮጵያና በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ያላቸውን ንቀት ያሳያል ብሎአል። ዘገባውን ከተመለከተ በሁዋላ ህመም እንደተሰማው የገለጸው አብዱላሂ፣ አስከሬን እንዲለቅሙ ሲገደዱ የነበሩት ሲቪሎች ሁኔታ በእጅጉ እንደረበሸው ገልጿል አንዳንድ የመንግስት ደጋፊዎች ኦብነግ አካባቢውን ለመገንጠል የሚንቀሳቀስ በመሆኑ፣ በአባለቱና በደጋፊዎቹ ላይ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው በማለት በማህበራዊ ድረገጾች ላይ ሲጽፉ ተመልክተናል፣ ለዚህ ምን አስተያየት አለህ የተባለው አብዱላሂ፣ " ይህን የሚሉ ሰዎች ማፈር አለባቸው በማለት መልሷል ወጣት አብደዱላሂ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን አስወግደው በአንድነት በመነሳት በስልጣን ላይ ያለውን ሃይል ማስወገድ እንደሚገባቸውም አብዱላሂ መልእክት አስተላልፏል። የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻ አውጭ ግንባር /ኦብነግ የአማርኛ ክፍል ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ ሃሰን አብዱላሂ በበኩላቸው፣ በክልሉ የሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት የቆየ መሆኑን ገልጸው፣ ድርጅታቸው በደቡብ አፍሪካ፣ በሄግ፣ በስዊድንና በጄኔቫ ጉዳዩ ተጣርቶ ተጠያቂ የሚሆኑት ባለስልጣኖች በህግ እንዲጠየቁ አቤቱታ ማቅረባቸውን ገልጸዋል።መንግስት የተገደሉት የኦብነግ አባላት እንጅ ሲቪሎች አይደሉም በሚል ለማስተባበል ቢሞክር የእናንተ ምላሽ ምን ይሆናል ተብለው የተጠየቁት አቶ ሃሰን፣ መንግስት በራሱ የሚተማመን ከሆነ አካባቢውን የጦር ቀጠና ማድረጉን ትቶ ለውጭ ጋዜጠኞችና የሰአብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ክፍት በማድረግ አለበት በማለት፣ በክልሉ የሚፈጸመው ጥቃት በህዝቡ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ተናግረዋል።

## የሶማሊ ክልል ፕሬዚዳንት ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ አልሆኑም

አቶ አብዲ ሙሃመድ 7 የስራ አስፈጻሚ የኮሚቴ አባላትን ማበረራቸውን ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ በአስቸኳይ እንዲመጡ ቢታዘዙም፣ የቀረበላቸውን ጥሪ ባለመቀበል ጅጅጋ ውስጥ እንደሚገኙ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ምንጮች ተናግረዋል።

ለአቶ አብዲ ቅርበት ያላቸው የመከላከያ ባለስልጣኖች በተደጋጋሚ ስልኮችን በመደወል አቶ አብዲን ለማግባባት እየሞከሩ ሲሆን አቶ አብዲ በበኩላቸው " ኢትዮጵያ ውስጥ 30 መንግስት ነው ያለው እንዴ?" በማለት እስከመጠየቅ መድረሳቸውንና ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ታውቋል። በሌላ በኩል ድሬዳዋ ላይ ተሰብስበው አቶ አብዲን ከስልጣን ማንሳታቸውን ያስታወቁት 7 የስራ አስፈጻሚ አባላት ከፌደራል መንግስት በደረሳቸው ጥሪ መሰረት አዲስ አበባ መግባታቸውን ምንጮች ገልጸዋል። አቶ አብዲ የስራ አስፈጻሚ አባላቱን ማባረር እንደማይችሉ ከፌደራል መንግስት ባለስልጣናት እንደተገለጸላቸው ታውቋል። በክልሉ ባለስልጣናት መካከል ያለው ሽኩቻ እየቀጠለ ባለበት በዚህ ጊዜ አቶ አብዲ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ምክንያቶች ያሰሩዋቸውን ሰዎች እየፈቱ ነው። በየረር ባሪ የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ በልዩ ሚሊሺያ አባላት ከተገደሉት 50 ሰዎች ጋር በተያያዘ ከታሰሩት 19 የአገር ሽማግሌዎች መካከል 17 ቱ በፕሬዚዳንቱ ልዩ ትእዛዝ መስከረም 4 ቀን ከምሽቱ 3 ሰአት ላይ እንዲፈቱ ተደርጓል። 2ቱ የአገር ሽማግሌዎች ቀደም ብሎ እስር ቤት ውስጥ መሞታቸውን ኢሳት መዘገቡ ይታወሳል። የአገር ሽማግሌዎቹ ኢሳት ጉዳያቸውን በመከታተሉም ምስጋናቸውን ገልጸዋል በክልሉ ውስጥ የሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተባብሶ መቀጠሉን ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

## ወያኔ በ 2007 ዓ.ም ለሚደረገው ሃገራዊና ምርጫ ለሚሊሻዎች ልዩ ተልዕኮ ሰጣቸው

በ2007ዓ.ም ለሚደረገው ሃገራዊና ክልላዊ ምርጫ ህብረተሰቡ ለተለያዩ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ድምፁን እንዳይሰጥ ለማፈን በሚያስችል ሁኔታ በክልሉ የሚገኙ ሚሊሻዎች ልዩ ተልዕኮ እንደተሰጣቸው ተገለጸ የአማራ ብሄራዊ ክልል መንግስት ሚሊሽያ ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ መኳንንት መልካሙ ሰሞኑን ለታማኝ አመራሮች በሰጡት ድርጅታዊ መግለጫ ላይ በያዝነው ዓመት በሚካሄደው ምርጫ ህዝቡ የተለያየ ፅንፍ በመያዝ ገዢው ፓርቲ ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ችግሮችን በማስወገድ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ ለማድረግ የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

አቶ መኳንንት ባለፈው ዓመት ለዚሁ ልዩ ተልዕኮ ከ360 በላይ ለሆኑ የሚሊሽያ አመራሮችና ባለሙያዎች በሁለት ዙር ፤ በወረዳ ደረጃ ላሉ የሚሊሺያ አባላትም ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሁለት ዙር ስልጠና መሰጠቱን ተናግረዋል፡፡ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ከ3 ሺህ 600 በላይ በሆኑ ቀበሌዎች ላሉ የሚሊሽያ አባላትም ልዩ ተልዕኮውን እንዴት ማሳካት እንደሚችሉ የሚያግዝ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን ምክትል ሃላፊው ለታማኝ የስርአቱ ደጋፊዎች ገልጸዋል፡፡ በክልሉ ያሉ የሚሊሽያ አባላት ከህዝቡ የተወጣጡ እና የገዢው መንግስት ደጋፊዎች መሆናቸው ስለሚታመን ጠዋትና ማታ ከህብረተሰቡ ጋር በመገናኘት በየቀበሌው ካሉ ልዩ ልዩ የወጣት፣ የሴቶች እና የአርሶ አደሩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም የመራጩን ህዝብ አመለካከት የመቀየር ስራ እንዲሰራ መታዘዙን፣ ይህ አሰራር ህዝቡ ታማኝነቱንና ድምጹን ለገዢው ፓርቲ የሚሰጥ መሆኑን የማረጋገጥ ሂደቱን ሊያሳካ ይችላል ተብሎ እንደታመነበት ለታማኞች ተናግረዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡትን ስልጠናዎች ለማካሄድ ከ22 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የጠየቀ ቢሆንም፣ ከዚህ ወጪ ውስጥ ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ህብረተሰቡ እንዲሸፍን መደረጉን፣ ገንዘብ በእጁ የሌለው ድሃው ህብረተሰብ ሳይቀር በግ ፣ ፍየል ፣ ዶሮና እህል እንዲያዋጣ በማድረግ ለሚሊሺያው ስልጠና መሰጠቱን ባለስልጣኑ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይም ተመላሽ ከሆኑ ወታደሮች ውስጥ የተሻለ የድርጅት ፍቅር ያላቸውን በመለየት ወደ ሚሊሽያው የመቀላቀል ስራ እየተሰራ እንደሆነ በዚሁ ዝግ ውይይት ተናግረው ፣ ወታደሮቹ በየገጠር ቀበሌው ሲሰማሩ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ከአርሶአደሩ ሊያገኙ የሚችሉበትን አሰራር ለመዘርጋት ግፊት የማድረግ ሃሳብ ወደ አመራሩ ዘንድ እንደወረደም አስረድተዋል፡፡

አቶ መኳንንት የግልና የመንግስት ተቋማት ጥበቃዎችና ሚሊሺያው ከላይ እስከታች የአመለካከት ችግር ያለባቸው በመሆኑ እና ተልዕኮ የሚሰጣቸው ከጸረ ሰላም ሃይሎች በመሆኑ ለአካባቢው ልማት ጠንቅ መሆናቸውን ገልጸዋል። ተከታትለው አንዳንድ ርምጃዎችን ለመውሰድ በአመራሩ መካከል መግባባት ላይ መደረሱንም ተናግረዋል፡፡ ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ በዳንግላ ዙሪያ ወረዳ የሚገኙ አንዳንድ አመራሮችና የሚሊሺያ አባላት ሚሊሺያው ከገዢው መንግስት ጥቅም ይልቅ የህብረተሰቡን ጥቅም በማስቀደም ከታሪክ ተወቃሽነት ነጻ እንሆናለን ብለዋል። የድምጽ መረጃውን ለላኩልን የሚሊሺያ አባላት ምስጋናችንን እንገልጻለን።

## አለም አቀፉ የግንቦት 7 "ላንች ነው ኢትዮጵያ" ዝግጅት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንደነበሩም ንቅናቄው አመልክቷል። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የጀመሩትን የነፃነት ትግልም ከዳር ለማድረስ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ተዘጋጅተናል በማለት በብዙ ሺ ዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአባልነት እንዲሁም በደጋፊነት መመዝገባቸውም ተመልክቷል። እየተካሄደ ላለው የአገር አድን ትግል ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የገንዘብ ድጋፍ መሰብሰብ መቻሉንና ኢትዮጵያውያኑም ድጋፋቸው ቀጣይነት እንዳለው ቃል ኪዳን በመግባት ማረጋገጣቸውን ለማወቅ ተችሏል። ንቅናቄው ለዝግጅቶቹ ስኬታማነት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ወጣ ውረዶችን ሁሉ ተቋቁመው እውን ላደረጉት ቆራጥ አባላቱና በነቂስ በመውጣት በየዝግጅቶቹ ላይ በመታደም የትግሉ ደጀን መሆናቸውን ላስመሰከሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በየዝግጅቶቹ ላይ ለመታደም ባይችሉም ድጋፋቸውንና አጋርነታቸውን በተለያዩ መንገዶች ለገለፁ የትግል ጓዶች ሁሉ ምስጋና አቅርቧል።

በተጨማሪም በየ አህጉራቱ በተሰናዱት ዝግጅቶች ላይ ሕዝባዊ ተቃውሞን፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እና ሕዝባዊ አመጽን በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር በሚቻልባቸው ስልቶች ላይ ከኢትዮጵያውያንን ጋር ስምምነት ላይ መደረሱን ያመለከተው ግንቦት 7 በተለይ በአገር ቤት የሚኖሩ ወገኖቻችን ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለሚነድፋቸው የትግል ስልቶችና ጥሪዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በንቃት በመከታተል በተቀናጀ ሁኔታ ምላሽ በመስጠት የትግሉ ዋና ደጀን ሆነው መቀጠል መቻላቸውን በድጋሚ ማረጋገጥ እንዳለባቸው ጥሪ አቅርቧል። ግንቦት 7 በተለይ ከወጣቱ፤ ከመከላከያ ሰራዊቱ፤ ከፖሊሱ፤ እንዲሁም በተለያዩ ተቋማት እያገለገሉ ካሉ ግለሰቦች እየተስተዋለ ያለው የውስጥ አርበኝነት የትግል ድጋፍና የትግል አጋርነት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም አመልክቷል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አዲሱን ዓመት አስመልክቶ . . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

## አለም አቀፉ የግንቦት 7 "ላንች ነው ኢትዮጵያ" ዝግጅት

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

በመጨረሻም ንቅናቄው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የተደላደለ ኑሮዋቸውን እና ቤተሰባቸውን በለንደን ጥለው ለኢትዮጵያ ነጻነትና ለሕዝቦቿ ፍትሕን ፍለጋ "ለአንቺ ነው አገሬ" የሚለውን ዝማሬያቸውን እያዜሙ ከሞት ጋር ፊት ለፊት ተፋጠው ለዓመታት ሲታገሉና ሲያታግሉ የኖሩ የነጻነት ታጋይ መሆናቸውን በመግለፅ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የአንድነታችን ቸቦ ሆኖነው ለአገራቸው ክብር፣ ለሕዝባቸው ነጻነት እንደ ሻማ እየነደዱ ያሉ የነጻነት ሓዋርያና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ናቸው፤ ለእኛ ለነጻነት ናፋቂዎችና ለአንድነት ኃይሎች ደግሞ በክፉ ቀን ያገኘነው የድል ፈር ቀዳጅ ጀግናችን ነው በማለት የንቅናቄያችን አርበኛ የጀመረውን ትግል ከዳር ለማድረስ በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንገኛለን በማለት አሁንም በጀመርነው በዚህ የተግባር አመት በአገር ቤትም ሆነ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እያሳዩ ያሉትን ድጋፍና አጋርነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክረ መቀጠል እና ከንቅናቄያንው ጎን በመሰልፍ የኢትዮጵያን ትንሳኤ እናፋጥን ዘንድ ይሁን ሲል ንቅናቄው በድጋሚ መልዕክቱን አስተላልፏል።

## የኦጋዴን ኡኡታ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሳይሆን ሞተንም እየሰደቡንና እያዋረዱን የሚደሰቱ አርዮሶች መሆናቸዉን በተግባር አረጋግጠዋል።

ይህ በኦጋዴን ወንድሞቻችን ላይ የሚደርሰዉ በደልና የጅምላ ግድያ እኛን አይመለከትም የምንል ኢትዮጵያዊያን ካለን እጅግ ባጣም ተሳስተናል። ወያኔ አዲስ አበባ ዉስጥም ኦጋዴን ዉስጥ ሠላማዊ ዜጎችን ሲገድል ለእኛ ተራዉ እስኪደርሰን ድረስ በህይወት ላለነዉ ኢትዮጵያዉያን የግድያዊ ቦታና የሟቹ ማንነት ምንም ልዩነት የለዉም። አዲስ አበባም፤ ኦጋዴንም፤ አምቦም ወዘተ የምንገደለዉ እኛዉ ኢትዮጵያዉያን ነን: ይንን ግድያና ዉርደት በቃ ብለን በተባበረ ክንድ ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን ማስወገድ ያለብንም እኛዉ ኢትዮጵያዉያን ነን።

ከኦጋዴን ክልል ዉጭ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ፍላጎት ሠላም፤ ፍትህ፤ ነጻነት' እኩልነትና ብልጽግና ነዉ፤ አርግጠኞች ነን የኦጋዴን ወገኖቻችን ፍላጎትም ከዚህ የተለየ አይደለም። ወያኔ በዘር፤ በቋንቋና በሐይማኖት ከፋፍሎን እንዳሰኘዉ እያሰረን፤ እየደበደበንና እየገደለን ለሃያ ሦስት አመት በላይ የዘለቀዉ ስላልታገልነዉ ወይም አሜን ብለን አንገታችንን አቀርቅረን ስለተገዛንለት አይደለም፤ ሁላችንም ወያኔን ለማስወገድና የናፈቀንን የነጻነት አየር ለመተንፈስ አቅማችን የፈቀደዉን ሁሉ አድርገናል። ሆኖም ወያኔ ገመናችንን አንድ በአንድ የሚያዉቅ አገር በቀል ጠላት ነዉና ድካማችንና በሚገባ ያዉቃል። እስከዛሬ የሚያሰቃየብም ደካማ ጎናችንን ስለሚያዉቅና ይበልጥ ደካሞች ሊያደርገን ቀንና ማታ ስለሚሰራ ነዉ። ዛሬ ይህንን ወያኔ በግልጽ የሚያዉቀዉን ድካማችንን ለማስወደግድና እነዚህን ዘረኞች ለማንቀጥቀጥ ለወያኔና ለቅጥረኞቹ መለያየትን፤ጎራ ለይቶ እርስ በርስ መናከስንና አንዳችን ስንበደል ሌሎቻችን ቀመን መመልከትን እምቢ ማለት አለብን። እነዚህ ሦስት ነገሮች በፍጥነት ማድረግ ከቻልንና ፍትፍ፤ ነጻነትና እኩልነት አስተባብረዉን ወያኔን በአንድነት ከታገልነዉ ወያኔ ከአንድ ሳምንት ትገል የማያልፍ ደካማ ጠላት ነዉ።የወያኔ ጥንካሬ የኛ መለያየትና እርስ በርስ መበላላት ብቻ ነዉ። ወያኔን አንድ ሆነን በጋራ ከታገልነዉ የመሳሪያ ጋጋታ አያስፈልገንም፤ አንድነታችን ብቻ ገፍቶ ይጥለዋል፤ተለያይተን ሁላችነም በየፊናችን ከታገልነዉ ግን እስካፍንጫችን ብንታጠቅም እያቆሰልነዉ እኛም እንቆስላለን እንጂ አናሸንፈዉም። ስለዚህ ዛሬ የኦጋዴን እልቂት እንዲቆም፤ የጋምቤላ መሬት ሽያጭ እንዲያበቃ፤ የአማራ፤ የአፋርና የሙርሲ ህዝብ መፈናቀል ባስቸኳይ እንዲቆምና አገራችን ኢትዮጵያን በማዕከል በጋራ እየመራን በክልል ደግሞ እራሳችንን በራሳችን ማስተዳደር እንድንችል ሁላችንም በአንድነት በወያኔ ላይ ክንዳችንን እናንሳ!!